የረቡዕ ጥቅምት 2 1998 ዓም ( ኦክቶበር 12 2005)

# የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ዕናት እየታየ ጎራው እየለየ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከአንድ የታሪክ ምዕራፍ ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ ከአለፈው የግንቦት ወር ጀምሮ የትግሉን ሰይፍ ወደ አፎቱ ያላስገባው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ አሻፈረኝ ባይነቱንና ለዘረኞችና ጠባብ አሁንም ሊገዛ የማይመች መሆኑን በድጋሚ ለማረጋገጥ በቅቷል፡፡ ድምፄን የነጠቀኝን የመለስ ዜናዊን ወንበዴ ቡድን አስወግዳችሁ ከአምባገነን ጭቆና አላቅቁኝ ቢላቸውም፥ አንድ አንድ የድርጅት መሪዎች፥ በወያኔ ህገወጥ ፓርላማ ለመግባት ወስነውበታል፡፡ ይህንን ዕርምጃ በመውሰዳቸው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር፥ ተከፍቶባቸዋል፥ ታዝቧቸዋል፥ንቋቸዋል፥ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ማንነታቸውን አውቋቸዋል፡፡ ኢትዮጵያና ሕዝቧ እስካሉ ድረስም፥ ይህ ብሔራዊ ክህደትና አሳፋሪ ተግባር በመጥፎነቱ ሲዘከር ይኖራል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለፖለቲካ መሪዎች ያለውንም አመለካከትና ዕምነት፥ በመሠረታዊ መልኩ እንደገና እንዲመረምርም አጋጣሚ ሆኖለታል፡፡ ማንነት እየታየ፥ ጎራው እየለየ መጥቷል!

አሁንም እንደ ትላንቱ፥ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሰማይ ከጭጋግ የነፃ ባለመሆኑ፥ የመጨረሻው ወሳኝ የሆነው የኢትዮጵያ ትግል ነፋስ፥ ጭጋጉን እስኪያጠራው ድረስ በዚሁ ዓይነት መቀጠሉን አያቆምም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና የዓባይ ወንዝ ከጉዟቸው ሊያቆማቸው ፤ሊገድባቸው፥ አጭጣጫቸውን ሊለውጣቸውና ሊቋቋማቸው የሚችል ኃይል ስለማይኖር፥ በጉዟቸው ላይ የሚጋረጠውን ሁሉ እየጣሱ ከመሄድ አይገቱም፡፡ የመጨረሻው ጉዟቸው መዳረሻውን ካላረጋገጠ በቀር፥ ይቆማሉ ብሎ ማሰብ፥ ራስን መደለል ይሆናል፡፡ ይህንን ታሪካዊ ክስተት መገንዘብ ከተቻለ፥ በወያኔ ፓርላማ ተገባ አልተገባ ትርጉም የለውም፡፡ በመሆኑም፥ ማን በወያኔ ፓርላማ ገባ ? ማንስ አልገባም? እያሉ ጊዜን ማጥፋት፥ የመለስ ዜናዊን ቡድን ጊዜ እንዲያገኝ ይረዳው እንደሁ እንጅ፥ ለትግሉ የሚያመጣው ርባና የለውም፡፡ የትግሉ ምዕራፍ በአዲስ ገፅ ቢከፈትም፥ ይህንን የትግል ታሪክ ምዕራፍ ባሸናፊነት ለመወጣት፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጎን በመቆም ከመታገል የተለየ ሌላ አማራጭ አይኖርም፡፡ በዚህ ፈታኝና መስቀለኛ የታሪክ ምዕራፍ ላይ በመሆናችን ሳቢያ፥ ከመቸውም በበለጠ ፥ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለንን ታማኝነት በአይበገሬነት ማረጋገጥ አለብን፡፡

በዓላማቸው በመፅናት፥ የሕዝቡን ትግልና ዕምነት አክብረውና ጠብቀው ከነመለስ ጋር ያለተደራደሩትን ድርጅቶች አይበገሬነት፥ እንደ አክራሪ - ዕንፈኝነት፥ ግትርነት ወዘተ.. አልፈው ተርፈውም እንደ ሞኝነትና ኋላ ቀርነት ይቆጥሩታል፡፡ የራሳቸውን የተንበርካኪነት አቋም ለመሸፈን የሚጠቀሙበት

የመፅናኛ ማጠየቂያ መሆኑ አይደንቀንም:: መለስና ግብረ-አበሮቹም፥ የአይበገሬነት አቋምን ይዘው የሚታገሉትን፥ እንደጦር ይፈሯቸዋል:: እንደአባታቸው ገዳይም ይጠሏቸዋል:: ፍራቻና ጥላቻ አንድ ላይ ከተባበሩ ደግሞ፥የቱን ያህል ጥፋት እንደሚያስከትል መገመት አያስቸግርም:: አይበገሬዎቹ የተንበርካኪዎችና የነመለስ ዜናዊ ቀደምት ዒላማዎች የሚሆኑትም፥ ለዚህ ነው:: በየትኛውም የታሪክ አጋጣሚም ይሁን፥ በማነኛውም ሥርዓተ-ማኅበር፥ ተውገርጋሪዎችና ተሸናፊዎች እንደሚኖሩ ሁሉ፥ በአንፃሩ ደግሞ፥ እስከመጨረሻው፥ ከቆሙበት ዓላማና ከገቡበት ሕዝባዊ ቃል ኪዳን ንቅንቅ ሳይሉ፥ትግሉን የሚገፉ፥አይበገሬዎች ነበሩ፥ አሁንም አሉ:: ወደፊትም መኖራቸው አይቀርም:: ሕብረተሰብና ትግል እስካሉ ድረስ ይህ ክስተት ይቀጥላል:: አይበገሬነት የአይበገሬዎቹ ልዩ ባኅርይና ተግባር በመሆኑ፥ የሁለቱ ተዋኅዶ እስከ መጨረሻው በኅብረት መዝለቅ፥ የተነሱበትን ዓላማ ለመፈፀም ያስችላል:: እስከ መጨረሻው በፅናትና በአይበገሬነት መታገል፥ ለመጨረሻው ሕዝባዊ ድል ወሳኝ ነው:: ይህ ሀቅ ባይኖር ኖሮ፥ ቅኝ ገዥዎች፥ ጨቋኝ ሥርዓቶች፥ ሀገር ወራሪዎች፥ አምባገነን መሪዎችና፥ ወዘተ.. ዘለዓለም እንደገዙ፥ እንደወረሩና እንደጨቆኑ በቀሩ ነበር:: በአይበገሬዎቹ ኢትዮጵያውያን/ያት አንድነት፥ ጀግንነትና ቆራጥነት፥ ብሎም፥እስከ መጨረሻው የትግል ዓላማ ፅናት፥ ወራሪዎች ተባርረዋል፥ አምባገነኖች ተወግደዋል፥ ቅኝ ገዥዎችም ድል ሆነዋል:: ይህ ባይሆን ኖሮ ሀገራችን ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነፃነት ጮራ የሚል ስም ባላተረፈችም ነበር:: አይበገሬነት የትላንትናው ጀግና ትውልድ የግል መለያ ሆኖ ቢቆይም፥ የ66ቱ ዓብዮተኛ ትውልድም ፥ የእነርሱን ባኅርይና ዓላማ ወርሶ እጅግ ከባድ መሥዋዕት መክፈሉ የቅርብ ትዝታ ነው:: የነዚያን ሰማዕታት ጓዶቻቸውን ክቡር አደራ ተቀብለው ትግሉን የቀጠሉት አይበገሬዎች፥አሁንም ወይ ፍንክች ባዮች ናቸው:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል በማዳፈን፥ የሀገራቸውን ዘላቂ ጥቅም ወደጎን በመተውና መርኃ ግብራቸውንም በመሸጥ የታሪክ ተወቃሽና የትውልድ መዘባበቻ አይሆኑም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስከሚጎናፀፍ ድረስ ትግላቸውን ይቀጥላሉ:: ይህን የማይታበል ቃላቸውንም ከሕዝቡ ጎን በመቆም በተግባር ያረጋግጣሉ::

ከዚህ መሠረታዊ የትግል ዓላማ በመነሳት ነው፥ እንግዲህ እኛ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ለመገምገምና ብሎም ወደፊት ምን መደረግ አለበት ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት የምንሞክረው:: ይህን ለመመለስ ደግሞ የአሁኑን ተባጭ ሁኔታ መገምገም የግድ ይላል:: በአሁኑ ወቅት:-

1) ወያኔ፥ በምዕራባውያን የበላይ ጠባቂዎቹ አማካኝነት እንደገና ለአምስት ዓመታት ኢትዮጵያን ለማጥፋት ፈቃድ ተሰጥቶታል::

2) የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ተነጥቆ ለነመለስ ዜናዊ እንዲሰጥ ሆኗል::

3) የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግልና ዕምነት ወደጎን በመተው÷ የተወሰኑ የተቃዋሚ ክፍሎች በወያኔ ፓርላማ ለመግባት ወስነዋል:: ይህ እርምጃቸው በትግሉ ላይ የሚያመጣው አንደምታ ወደፊት የሚታይ ይሆናል::

4) የሕዝቡን ትግል በመደገፍና ሀገራዊ ቃል-ኪዳናቸውንም በማክበር÷ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፍው ትግሉን ለመቀጠል የወሰኑ በርካታ ድርጅቶች አሉ::

5) ሀቁ ቀደም ብሎ የታወቀ ቢሆንም÷ በተለይ ግን÷ ከግንቦቱ ምርጫ ወዲህ÷ ሀገራችን÷ የምዕራባውያኑ የእጅ አዙር ቅኝ ተገዥ መሆኗ እንደገና በተጨባጭ ተረጋግጧል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የምዕራቡ የእጅ አዙር ቀኝ ተገዥነትን የሚቀበል አይሆንም:: በመሆኑም ትግሉን አጠናክሮ ለነፃነቱ ይታገላል:: የተያዘው ትግል በአመዛኙ የነፃነት ትግል ነውና!

6) በአንድ በኩል÷መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ÷ በሌላ በኩል ደግሞ ምዕራባውያኑ የጡት አባቶቻቸው÷ ለጊዜው የአቀዱት ዓላማ በሙኑም ቢሆን የተሳካላቸው መስሏቸዋል:: ይህ ግን ለብዙ ጊዜ የሚቀጥል አይሆንም:: ነገ በኢትዮጵያ ሕዝብ ቆራጥ ትግልና ድል እንደሚከስም ጥርጥር ሊኖር አይችልም:: ይህ ደግሞ ለሥነ-አዕምሮ ዕፎይታና ፍጆታ የሚነገር ነባቢት ሳይሆን÷ነገ በተግባር ተተርጉሞ የሚረጋገጥ ይሆናል::

ይህን ነባራዊ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ለመዳሰስና ለመገንዘብ ከቻልን÷ ከእንግዲህ ምን ማድረግ አለብን? የሚለውን ማማተር ሊኖርብን ነው:: በመሆኑም:-

1) ከሁሉ አስቀድሞ ማን ፓርላማ ገባ ማን ቀረ ወደሚለው ጉንጭ-አልፋ ክርክር መግባት ያለብን አይመስለንም:: በዚህ እንደ ጠዋት ጤዛ ረግፎ በሚያልፍ ሰሞነኛ ወሬ ሳንጠመድ÷ ስለ ወደፊቱ የትግል ተግባራችን ላይ ማተኮር አለብን:: በመሆኑም:-

2) ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጎን ለመቀጠል የወሰነው የተቃዋሚ ጎራ÷ እንደገና ኃይሉን በማሰባሰብ ጠንክሮ መውጣት አንገብጋቢና አጣዳፊ የትግል ዕቅዱ ወይም አጀንዳው ሊሆን ይገባል::

3) የሀገሪቱን ስትራተጃዊ ወይም ቋሚና ዘላቂ ጠላትና ወዳጅ በመለየትም አዲስ የኃይሎችን አሰላለፍ ማረጋገጡ÷ ይዋል ይደር የሚባልበት አይደለም:: በታክቲክም ይሁን በስልት ደረጃ ወዳጅ ጠላትን ለይቶ ማወቅና በየፈርጁ ማስተናገድ÷ ለመጨረሻው ድል ዋስትና መሆኑ አያከራክርም::

4) የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመረው ትግል በአቸናፊነት እንዲጠናቀቅ ከተፈለገ÷ በአዲስ ኃይል ተጠናክሮ ሊወጣ የሚችለው የተቃዋሚ ጎራ÷ ሊያሰባስበው በሚችለው ስትራተጃዊ ዓላማና ብሔራዊ ራዕይ ላይ የተመረኮዘ

የትግል አጀንዳ በመንደፍ፥ የሕዝቡን ትግል መምራት ይጠበቅበታል። እስካሁን ድረስ ይህ ባለመሆኑ፥ ውጤቱ ይኸው የወያኔን ጊዜያዊ ድል ተብዬ ሊያስከትል ችሏል። ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ፥ ትግሉ በማያሻማ ዓላማና ግብ ላይ በተመሠረተ፥ ብሎም ቆራጥነት፥ ታማኝነትና ችሎታ ያለው አመራር ሊሰጥ በሚችል ኃይል መመራት አለበት። እስካሁን ይህ አልነበረም። በአንፃሩ ግን፥ ሕዝቡ መሪ፥ ድርጅቶች ተመሪ ሆነው የቆዩበት ሁኔታ ነበር የነበረው። ይህንን መካድ፥ ማለት አሁንም ከስህተት ለመመማር ዝግጁ አለመሆን ነው።

5) የተለያየ የኅብረተሰብ ክፍል፥ በትግሉ እንዲሳተፍ ማድረግ የሚያጠያይቅ አይደለም። ምሁራንን ማሳተፍ ወሳኝ ነው። ሲቪል ኅብረተስብ፥ የሙያ ማኅበራት፥ ጋዜጠኞች ደራስያን፥ ተማሪና መምህራን፥ ሴቶች፥ የሃይማኖት ተቋማት፥ አጋርነትና ተሳትፎ ከሌለ ትግሉ ተልፈስፍሶ ከመቅረት የሚያድነው የለም። ሰርቶ አደሩና አርሶ አደሩ ደግሞ የትግሉ ማዕከል መሆኑን ማረጋገጥ የግድ ነው።

6) ከወያኔ መሰሪ ፕሮፓጋንዳ፥ ከጠላት ሰርስሮ መግባት፥ ከባዕዳን ጣልቃ ገብነትና ፥ በብሄረሰብ ለመከፋፈል ከሚጠነሰሰው አጥፊ ሴራ ወጥመድ ሳይገቡ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም፥ በሀገር አንድነትና በዜጎቿ እኩልነት ዙሪያ ተሰባስቦ መታገል መተኪያ የሌለው ብቻ ሳይሆን፥ የመጨረሻው ድል ማስገኛ ፍቱን መሳሪያ መሆኑን አምኖ በመቀበል ሕዝባዊ ሰላማዊ አመፁን ማቀጣጠል፥ አይቀሬና ታሪካዊ ነው።፡

አሁን፥ ሀቁ እየታየ፥ ጎራው እየለየ፥ ትግሉ እየነጠረ፥ ዕውነት እየመሰከረ፥ በመሄድ ላይ ስለሆነ፥ ከሃዲው አፍሮ፥ ጠላት ከስሮ፥ ታሪክ ተከብሮ፥ ትግሉ ተጠናክሮ፥ ነገ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአቸናፊነት እንደሚወጣ ጥርጥር አይኖረንም።

ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፁ ይፋፋም!!
የስራ ማቆሙና የሙት ከተማ አድማ ዳግም ይጠራ!!
ህብረታችን ጠንክሮ ወደ ድል እንጓዝ!!